


# አለማ ካውዳይስ መኖ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ደረጃውን የጠበቀ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ግምባር ቀደም ዘመናዊ መኖ ማምረቻ ነው፡፡

## አለማ ካውዳይስ መኖ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከኔዘርላንዱ ድርጅት ዴሁስ ኢንተርናሽናል ጋር በጥምረት የሚሰራ ድርጅት ነው፡፡

ዴሁስ በኔዘርላንድ የሚገኝና በእንስሳት መኖ ማቀናበር ከ100 አመት በላይ የሰራ እና እየሰራም የሚገኝ በአለም ላይ በርካታ ፋብሪካዎች ያሉት ድርጅት ነው፡፡ አለማ ካውዳይሰ መኖ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከአጋር ድርጅቱ ከዴሁስ ኢንተርናሽናል ካለፉት 100 አመታት ካካበተው ልምድ በርካታ ዕውቀት በማግኘት ተጠቃሚ ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር የቀንድ ከብት ካላቸው ሃገራት ተርታ የምትሰለፍ በመሆኗ ከብት ማድለብ በአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍል የሚዘወተር የስራ ዘርፍ ነው፡፡ በአብዛኛው የከብት አድላቢዎች የቦረና ከብት ዝርያን የሚያደልቡ ሲሆን ከቦረና ከብቶች የሚገኘው ስጋም በኢትዮጵያውያንም በኤክስፖርትም ደረጃ በጣም ተፈላጊ ነው፡፡

ድርጅታችን አለማ ካውዳይስ መኖ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከብቶች በአጭር ጊዜ ደልበው ለገበያ እንዲደርሱ እና ትርፋማ እንዲሆኑ የሚያስችል የተመጣጠነ መኖ ያመርታል፡፡ ስለዚህ አለማ ካውዳይሥ መኖ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሚከተሉትን የመኖ አይነቶች ያቀርባል፡፡

- የጥጃ ማሳደጊያ ፔሌት መኖ
- የበሬ ማድለቢያ ቤዚክ መኖ
- የበሬ ማድለቢያ ሱፐር መኖ

### የጥጃ ማድለቢያ ፔሌት መኖ

ከብቶቻችሁን ከጥጃነት ዕድሜ ጀምራችሁ የምታሳድጉ ከሆነ በጥጃ ማሳደጊያ ፔሌት መኖ ተመራጭ የመኖ አይነት ነው፡፡ ይህ የመኖ አይነት ለጥጆቹ ዕድገት የሚረዳ ከፍተኛ መጠን ያለው ኃይል፣ፕሮቲን፣ቫይታሚን እና ማዕድናት በውስጡ ይዟል፡፡ ጥጃዎቹ ጥሩ ኮርማ ለመሆን እንዲዘጋጁ ፈጣንና ጤናማ ዕድገት ይሰጣቸዋል፡፡ በቀን 3ኪ.ግ የተመጣጠነ መኖ እና ድርቆሽና ውሃ ያለገደብ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

ከጥጃ ማሳደጊያ ፔሌት መኖ በኋላ ወይም የደረሱ ኮርማዎችን ማደለብ ስትጀምሩ በግባችሁ እና ባሉት አጠቃላይ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ 2 አይነት የበሬ ማድለቢያ መኖዎችን እናቀርባለን፡፡

### የበሬ ማድለቢያ ቤዚክ መኖ

የበሬ ማድለቢያ ቤዚክ መኖ ለትንሽ እና መካከለኛ መጠን ማድለቢያ ላላቸው ገበሬዎች ወይም ወቅታዊ የማድለብ ስራ ለሚሰሩ ገበሬዎች ተስማሚ የመኖ አይነት ነው፡፡ ይህ የመኖ አይነት በቀን የክብደቱን 3% ወይም ከ8-10ኪ.ግ ከድርቆሽና ሳር ጋር መመገብ ይኖርበታል፡፡ ከብቶቹ በበቂ ሁሌታ እንዲያድጉ ትክክለኛውን መጠን የተመጣጠነ ንጥረነገር በውስጡ የያዘ ሲሆን ትንሽ ወይም መካከለኛ መጠን ያለው አድላቢ ወይም ወቅታዊ አድላቢ ከሆናችሁ የበሬ ማድለቢያ ቤዚክ መኖ ትክክለኛው የመኖ አይነት ነው፡፡

## የበሬ ማድለቢያ ሱፐር

የበሬ ማድለቢያ ሱፐር መኖ ከብቶቻቸው በአጭር ጊዜ ለገበያ እንዲደርሱ ለሚፈልጉ አድላቢዎች ተመራጭ መኖ ነው፡፡ በአጭር ጊዜ መድረሳቸው በአመት ውስጥ ተደጋጋሚ ብዙ ጊዜ ለመስራት ይጠቅማል፡፡ ይህ የመኖ አይነት በውስጡ የተመጣጠነ እና ከፍተኛ መጠን ያለው ንጥረነገር ያለው ሲሆን ይህም ከፍተኛ ክብደት በአጭር ጊዜ ለማግኘት ያስቻላል፡ ፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ የመኖ አይነት በአጭር ጊዜ ለገበያ እንዲደርሱ በውስጡ ፕሪሚክስ ቫይታሚን ፣ ጠቃሚ ማዕድናትና ለዕድገት አፋጣኝ የሆኑ ንጥረነገሮች ይዟል፡፡ይህን የመኖ አይነት ለየት የሚያደርገው ነገር ሞናንዚን የተባለ ለዕድገት ጠቃሚ የሆነ ንጥረነገር በውስጡ የያዘ ሲሆን ይህም ንጥረነገር ከብቶች የሚመገቡት መኖ በከፍተኛ ሁኔታ ወደስጋነት እንዲለውጡ ያስችላቸዋል፡፡ ስለዚህ በአነስተኛ የመኖ ፍጆታ የሚጠበቀውን ውጤት ማግኘት ይቻላል፡፡

### በመሆኑም አብዛኛዎቹ አድላቢዎችና የውጪ ላኪዎች የበሬ ማድለቢያ ሱፐር መኖን ተማራጭ አድርገውታል፡፡

- ከብቶቻቸውን ከሚልኩባቸው ሃገራት የሥጋ ጥራት ላይ ከፍተኛ አድናቆት አግኝተዋል
- በአጭር ጊዜ ትልቅ ክብደት ያላቸውን ከብቶች ማግኘት ችለዋል፡፡
- ከብቶቹ በአጭር ጊዜ የሚደርሱ በመሆናቸው በአመት ውስጥ ብዙ ጊዜ እንዲሰሩ ያስችላቸዋል

የአላማ ካውዳይስ መኖ ኃ/የተ/የግ/ማህብረ የበሬ ማድለቢያ ሱፐር መኖ በአጭር የማድለቢያ ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ክብደት አስገኝቶልናል፡፡ ደንበኞቻችንም በስጋው ጥራት በጣም ደስተኞች ናቸው፡፡

- አቶ ገዛሃኝ እና ኮ/ል ግርማ  የከብት አድላቢና የውጪ ላኪዎች ከ አዳ

የበሬ ማድለቢያ ሱፐር መኖ መጠቀም ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ ከብቶቹ በጣም በፍጥነት ማደግ ጀምረዋል፡፡ባየሁትም ለውጥ በጣም ተደንቄአለው፡፡ ከብቶቹም በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ለውጥ አሳይተውኛል፡ ፡ ከብቶች ለገበያ የሚደርሱበት ጊዜ አጭር  በመሆኑም አነስተኛ የመኖ ፍጆታ ተጠቅሚያሀው፡

- አቶ እናዳለው የከብት አድላቢ

በአድላቢዎቹ ግብና ሁኔታ ላይ በመመስረት የበሬ ማድለቢያ ሱፐር መኖ ሙሉ ለሙሉ ወይም እንደ አጋዥ መኖ መጠቀም ይቻላል፡፡

### የበሬ ማድለቢያ ሱፐር መኖ ሙሉበሙሉ መጠቀም

በአጭር ጊዜ ክፍተኛ ክብደት ያላቸውን ከብቶች ማግኘት የምትፈልጉ ከሆነ የበሬ ማድለቢያ ሱፐር መኖን ሙሉበሙሉ ተጠቀሙ፡፡ ይህም ማለት በቀን የክብደቱን 3% ከ8-10ኪ.ግ የተመጣጠነውን መኖ እና ያለገደብ ውሃ እና ድርቆሽ በመስጠት መጠቀም፡፡

### የበሬ ማድለቢያ መኖ እንደ አጋዥ መኖ መጠቀም

lየከብቶቹን ፈጣን ዕድገት የምትፈልጉ ከሆነና ነገር ግን የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎችን የማግኘት ዕድላችሁ ሰፊ ከሆነ የበሬ ማድለቢያ ሱፐር መኖን እንደ አጋዥ መኖ መጠቀም ይቻላል፡፡ይህም ሲሆን በቀን ከ3-4ኪ.ግ የተመጣጠነውን መኖ እና በተጨማሪ ልታገኙ የምትችሏቸውን የተለያዩ ጥሬዕቃዎች መመገብ ይኖርባችኋል፡፡ ሁል ጊዜ ንፁህ ውሃ እና ድርቆሽ መኖር ይኖርበታል፡፡



### ለተሳካ የከብት ማድለብ ስራ ዋና ተግባራት

- የአለማ ካውዳይስን የተመጣጠነ መኖ መጠቀም
- በቂ የሆነ ከፀሃይ የሚጠለሉበት መጠለያ ማዘጋጀት
- ንፁህ ውሃ ሁል ጊዜ ያለገደብ መስጠት
- ድርቆሽና ጭድ ያለገደብ መስጠት
- የተመቻቸና ለስላሳ የሆነ(በአሸዋ ወይም በገለባ) የተሰራ ምቹ ማረፊያ ያስፈልጋቸዋል፡፡
- አስፈላጊውን ክትባት ማግኘት አለባቸው

**ALEMA KOUDIJS FEED PLC**

Ziquala Road, PO BOX 149 Debre Zeit, Ethiopia tel. 011 433 0662, 0930 2917 95/96, 09 3029 1772

sales@alemakoudijs.com

www.facebook.com/alemakoudijs

01/2016/KR